# <u>ምነዋ ባሻ ኬሌዎች ፈሉብን?</u>

ከአሰፋ ከበደ

በከርቸሌ ያለፈ ዜጋና ሕይወቱን በዚያ የተቀጠፈ ኢትዮጵያዊ ቁጥር ብዙ ነው። በየዓርቡ ስንቱ ተሰቅሏል። ስንቱ ንጹሕ ዜጋ ስሙ ተጠርቶ ወጥቶ በዚያው ደብዛው ጠፍቶ ቀርቷል። ለወራት ታስረው ወኔያቸው ተሰልቦ ማሪኝ አብዮቴ ብለው ጓደኞቻቸውን አሳልፈው የሰጡ ጥቂት አልነበሩም። ዓመት ታስረው ስንቱን ለሞት ዳርገው ለሞስኮ ነጻ ትምህርት የበቁትንም እናውቃቸዋለን። ወይኔ ከርቸሌ!!! የዚያ መከራ ቦታ ሰለባዎች ዝምታን ጥላችሁ ምስክር ሁኑ እስቲ!! ስንቱን መከራ ተቀብለው ጸንተው የቆዩንትም ማወደስ ተገቢ ነው። የመራራ ጉዲና ዓይነቶቹም ለከርቸሌ የዳረጋቸው ጸረ ሕዝብ ሚናቸው ቢሆንም፣ ታስረን መከራ ተቀብልን ብለው ግና የከዱ ሆነው ሳለ፣ በጽናት ታስረውም መከራም የተቀበሉትን ጀግኖች ዛሬም ከወያኔ ጎን ቆመው ያወግዙ የለ? ትግል በቃኝ ብለው፣ የግል ሕይወታቸውን ሲያደራጁ ዓመታት አስቆጥረው፣ ትግሉን በፅናት የቀጠሉ የሕዝብ ልጆችን ሊወነጅሉ የሚነሱም አሉ። ለትግሉ ነው ሕይወቴ ብሎ ቃልን አክብሮ መገኘት ወንጀል የሆነ ይመስል። ለመሆኑ “ኢትዮጵያ ሀገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ/የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ?!” የሚለው እንጉርጉሮ መቼ ይሆን የሚያቆመው?

የያኔ ከሀዲዎችና ቡከኖች ዛሬ ታሪክ ነጋሪ የጠፋ መስሏቸው የባጥ የቆጡን ሲቀባጥሩ ትዝ የሚሉኝ ባሻ ኬሎ ናቸው። የከርቸሌ ዋርድያ። የአያ ሽንቁጤን ለሌላ ጊዜ ልተወውና ባሻ ኬሎ የመጣልንን ምግብ

አካፍለን ሆዳቸው ሲሞላ ከቅዱስ ቅዱስ በላይ ሆነው “እናንት ጀግኖች” ሲሉንም ይዳዳቸው ነበር። ሆዳቸው ካልሞላ ግን የሰይጣን ሰይጣን ሆነው ያሰቃዩን ነበር። ባሻ ኬሎ ምን ይመስላሉ ቢባል መልሱ ሆድ ነው እንጂ ጠይም ከሲታ ወይም ወፍራም ቀይ የሚላቸው የለም። በሰው መልክ ቆመው የሚሄዱ ጉማሬ ነበሩ። ሆዳም--አድርባይ ነበሩና። አንተ ማነህ ሲሉት ሆድ የሚል ማስታውቂያ በዋሺንግተን ራዲዮኖች እንሰማ የለ? ባሻ ኬሎ ያ ናቸው። ሆድ ነኝ ባይ ሳያፍሩ።

ዛሬ ባሻ ኬሌዎች ፈልተዋል። ሆዳሞች ማለቴ ነው። ነጋ ጠባ አቋማቸውን ቀይረው ለሆዳቸው የሚያድሩ ግለሰቦች። ከርቸሌ ሳለን አይተናቸዋል። ዛሬም እርግጥ ነው በቃሊቲም ይኖራሉ። የትግል ጓዶቻቸውን አጋልጠውና አሳልፈው ሰጥተው የራሳቸውን ርባና ቢስ ሕይወት ያዳኑ። ዛሬ ግን ታሪካችን ተረስቷል ብለው የሚቀባጥሩ። እነዚህን ማወቅ መለየት ከባድ አይደለም። ያስፈሰሱት ደም ያቃዣቸዋል። ከሕዝብ ጎራ ያሉ መስለው ሳይውል ሳያድር ሰልፋቸው ከሀገርና ሕዝብ ጠላት ጎን ሆኖ ይከሰታል። እንደ ውሻ ወደ ትፋታቸው በፍጥነትም ይመለሳሉ። የትላንት ቃላቸውን ይክዳሉ። በአቋሙ የጸናውንም ሊያወድሙ ሊያጥላሉ ሲወራጩ ይታያሉ። ባሻ ኬሎ ሆዳቸው እስከሞላ ድረስ ፍራሽ ነበሩ። ሆዳቸው ካልሞላ ደግሞ የራበው ጅብ ሆነው አሰቃይተውናል። የምናስታውሳቸው በደግነታቸው ሳይሆን በሆዳምነታቸውና በክፋታቸው ነው። የዛሬም ባሻ ኬሌዎች ማንነታቸው የሚገለጠው በክህደታቸውና በሆዳምነታቸው ነው። ፕሮፌሰር አሥራት ነፍሳቸውን ይማር፣ መሬት ይቅለላቸውና በአስከፊ አድርባይነት ተማረው ሆዳም አ... ብለው ነበር። ባሻ ኬሌዎች በዝተውባቸው። አዝነውና ተበሳጭተው። በየድርጅቱና በትግል መስክ ባሻ ኬሌዎች

ፈልተዋል። ሆዳችንን ሙሉ ይሉናል-- ካልሞላንላቸው ያኮርፉሉ፤ ይርቁናል፤ አልፈውም ከጠላት ጎራ ይገባሉ። ዋሺንግተን ሲያኮርፉ ነግ ወያኔ ጋ አዲስ አበባ ናቸው። ካልሄዱም ባሉበት ለአሜሪካ እንግሊዝ አስካሪ--ባንዳ ወሬ አቀባይ ሆነው ያገለግላሉ። ታጋይ ሀገር ወዳድ ሀይሎችን ለመከፋፈልና ለማዳከም ይሰራሉ። ያደረሱትና እያደረሱ ያሉት ጉዳትም ቀላል አይደለም። ዜጎች ዓይናቸውን መክፈት አለባቸው።

ይህን ሁሉ ለመጻፍ ያነሳሳኝ ቅድም የገለጽኩት እንጉርጉሮ አድማጭ አግኝቶ ማቆም ስላለበት ነው። መልስ ማግኘት። ከሀዲዎች፣ ትላንት የቀይ ሽብር አራማጆች፣ የለገሰና መላኩ ተፈራ ካድሬዎችና ተሿሚዎች፣ የወያኔ አድራጊ ፈጣሪዎች ሆነው ከጎናችን የነበሩ የሕዝብ ልጆችን እንዳልጨፈጨፉ፣ ዛሬ ባፈሰሱት ደም ላይ ተረማምደው ታጋይ ተብለው ሲወደሱ፣ የሰማዕታቱ ብሶት ጎልቶ ይሰማል። የትግሉን ጎራ ሲያምሱና ሲረብሹ ሲታዘቡ፣ ዛሬም ሰማዕታታችን "ኢትዮጵያ ሀገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ/የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ!" እያሉ በእልህ ያንጎራጉራሉ። ለአፈሩ አፈር ሆነው የተሰውለት ወንዝ፣ ፈፋ፣ ሜዳ፣ ጋራ፣ ሸንተረርም ይህንኑ እንጉርጉሮ ከመልካ መልካ ያስተጋባል። የጀግናና ሀገርወዳድ፤ የሕዝብ መሪና አርበኛ ትርጉሙ በአፍጢሙ ተደፍቶና ተቀይሮ፣ የትላንት ወያኔዎች ሳይቀሩ የትግሬ ትምክህተኛ መሆናቸውን ሳይቀይሩ ሲወድሱ መስማቱ እጅግ ያስመርራል። ይህ ሁሉ በቃ አለፈ ደቀቀ ሊባል የሚገባው ነው። ወያኔ ንቆን ሀገርና ሕዝብን እያጠፋ በአስቃቂ ሽሙጥ ደርግ ለገደላቸው ሐውልት ብጤና ራሱን የሚያወድስበት ቤተ መዘክር አቁሚያለሁ እያለን ነው። ሰው ሆዱንና ውርደትን ከወደደ አሳማ ወይም እርያ ነው፤ እንሰሳ። ዓላማችን

ያሉትን ከመ ቅጽበት ሲከዱ፤ ድርጅታችን ያሉትን እያወገዙና አንጃ ገለመሌ እየሆኑ፤ ከአሊ ሀሰን እስከ ስዬ አብርሃን እያቀፉ፤ ለሕዝብ የሚታገሉትን እያጥላሉ በሕዝብ ትግል ላይ መጥፎ ታች በሌዎች ሁሉ ማንነታቸው ተጋልጦ መወገር ቢቀር መወገዝ አለባቸው። የሕዝብ ጎራ ይጽዳ ሲባል ይህ ጥሪ የሰው እንከቶዎችንና ባሻ ኬሌዎችን፣ አስመሳዮችን፣ ልበ ባንዳዎችን፣ ቁም አፎችን ሁሉ ማራቅ ያስፈልጋል ማለት ነው። ጎራ ካልጸዳ ክንድ ይዝላል። ከሀዲና ነፍስ ገዳይ፤ የሽብር አራማጅና ነፍሰ ገዳይ፤ ሀገር አጥፊ ወያኔን ሁሉ አቅፎ ወደፊት ወደ ድል መጓዝ አዳጋች ነው። ከእኔ በላይ ታጋይም አዋቂም፤ ምርጥም ልሂቅም የለም ብለው አብጠው ከትግሉ ፊርማታ ቁጥር አንድ ላይ ሳይደርሱ የሚፈነዱትንም አርቲ ቡርቲዎችንም ማግለል ተገቢ ነው።

ባሻ ኬሎ ሳይሞቱ የሚቅር አይመስለኝም። ለእሳቸውም ለወዲ ዜናዊም መሬት ይክበዳቸው። እንደ ሥራቸው ይስጣቸውና። የክፋትና የጥፋት ልጆቻቸው ግን ዛሬም ሊያስጨንቁንና በክህደታቸው ሊያደናቅፉን ከመሀላችን አሉ። ሆድ ሆድን እየወለደ። ታዲያ ዝምታው ለምን ነው? ሰው መሆን ከፈለግን ሰው ሰውን መውለድ አለበት። አሁንም ለሶስተኛ ጊዜ ልድገመውና "ኢትዮጵያ ሀገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ/የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ" ለሚለው የሕዝብ ልጆች እንጉርጉሮ ምላሽ መስጠት መቻል አለብን። ለሕዝብ ልጆች ሕዝባዊ ጋሻ መሆን። የትግሉን ተዋንያን ሕዝባዊነት፣ ቆራጥነት እና ፅናት በመለካት ለሁሉም እንደየሥራው መስጠት። ሚዳውንም ማጥራት። አለዚያ ሁልጊዜ "የአህያ ባል፣ ከጅብ አያስጥልም" እንዲሉ እየሆነ፣ የድል ዋዜማችንን እያስነጠቅን፣ ሀገርና ሕዝባችንን ለተደጋጋሚ ጥፋት እንዳርጋለን።